

## አይነ ስውሩ ሰው

- ኢየሱስ በሄደበት ስፍራ ሁሉ ብዙ ሰዎች  ይከተሉት ነበር። ይኸውም ዘመዶቻቸውንና ወዳጆቻቸውን ይዘው ሲሆን ምክንያታቸውም ኢየሱስ እንዲፈውስላቸው ነው። በዚህ ቀንም ኢየሩሳሌምን ለቆ እየወጣ ሳለ እንደወትሮው ብዙ ሕዝብ አጅቦት ነበር።

- ወደኢያሪኮ እየተቃረበ ሳለም አንድ አይነ ስውር በመንገድ ዳር ተቀምጦ ይለምን ነበር። ስሙም በርጠሎሜዎስ ይባላል።

- ይህ ሰው ኢየሱስ በዚያ እያለፈ መሆኑን ሲረዳ እንዲህ እያለ መጮኽ ጀመረ፣ “የዳዊት ልጅ ሆይ ማረኝ!” (ኢየሱስ የዳዊት ልጅ እየተባለ ይጠራ ነበር። ምክንያቱም  እስራኤልን ለ40 ዓመት ከገዛው የዳዊት ዘር ስለተገኘ ነው።)

- ታዲያ የአይነ ስውሩ ወዳጆች ፀጥ እንዲል ነገሩት። እርሱ ግን አብዝቶ መጮኹን ቀጠለ።

- ኢየሱስም ቆም አለና በርጠሎሜዎስን እንዲያመጡት ደቀመዛሙርቱን አዘዛቸው። እነርሱም፣ “አይዞህ በእግርህ ቁም። መምህሩ ና ይልሃል።” አሉት። እርሱም ከላይ የደረበውን ልብሱን ጣል አድርጎ ወደ ኢየሱስ መጣ።

- ኢየሱስ ምን እንደሚፈልግ ሲጠይቀው፣ “መምህር ሆይ ማየትን እሻለሁ።” ሲል መለሰለት።

- ኢየሱስም፣ “እምነትህ አድኖሃል።” አለው። ወዲያውም ማየት ቻለ። ኢየሱስንም ተከተለው።

- በኢየሱስ ክርስቶስ የመፈወስ ኃይል ላመነው ለዚህ አይነ ስውር እንዴት ያለ የደስታ ቀን ይሆን!

*. ይህ ኢየሱስ አይነ ስውሩን የሚፈውስበት ታሪክ የሚገኘው በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 18፡ 35 _ 43 እና በማርቆስ ወንጌል በምዕራፍ 10፡ 45 – 47 ውስጥ ነው።*

http://gardenofpraise.com